የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 39
ADDIS ABABA 12th May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፲፭/፪ሺ፫

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ........................................ገፅ ፭ሺ፰፻፳

**CONTENTS**

**Regulation No. 215/2011**

Assosa University Establishment Council of Ministers Regulation........................................ Page 5820

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፭ /፪ሺ፫

የአሶሳ ዩኒቨርሲቲን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲፭/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. መቋቋም

፩/ አሶሳ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል፡፡

*COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 215 /2011*

*COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ASSOSA UNIVERSITY*

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Assosa University Establishment Council of Ministers Regulation No. 215/2011".

2. *Establishment*

1/ Assosa University (hereinafter the "University") is hereby established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210./2011.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በአሶሳ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

3. Main Campus

The University shall have its main campus at Assosa and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 12th day of May 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት